የሰበር መ/ቁ. 19841

ሠኔ 30/1998 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አ/ማ - አልቀረቡም

**መልስ ሰጭ፡-** አቶ ፍቃዱ ኪዳኔ አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /Cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የህግ ነጥብ የሚመለከት ነው፡፡

የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ መ/ሰጭ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ በመቀበል አከራክሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔው ላይ ይግባኝ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ከላይ የተመለከተውን የህግ ነጥብ ሳይመረመር አልፎታል፡፡

አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 5/11/98

ችሎቱም ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ የሚቀርብ ክስ የክስ ምክንያት /cause of action/ አለው? ወይስ የለውም? የሚለውን የህግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ ያቀረበበትን ውሣኔ መርምሯል።

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 16273 ጥቅምት 22 ቀን 1998 በሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የህጉን ድንጋጌዎች በመተርጎም አንድ ሠራተኛ ከውሉና ከአሰሪና ሠራተኛ ሕጉ አንፃር ሊያገኘው የሚገባና የቀረበለት ጥቅም ካለ የቀረበት ጥቅም እንዲሰጠው መጠየቅ /ክስ ማቅረብ/ የሚችል ሲሆን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ ይወሰንልኝ ብቻ የሚቀርብን ክስ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድም ሆነ የሥራ ክርክር ችሎት ተቀብለው ሊያዩ የሚችሉበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

በዚህ ጉዳይም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ መ/ሰጭ ያቀረቡትን ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠርኩ/ን/ ይወሰንልኝ/ን/ በማለት ያቀረቡትን ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ውድቅ ማድረግ የነበረበት ሲሆን ጉዳዩን ተቀብሎ በማከራከር ውሣኔ በመስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል።

## ው ሣ ኔ

- የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ.ቁ. 211/01/95 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 30868 የሰጠው ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ተሽሯል።
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ ——— ቀን 5/11/9?